በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት

# ዜና ኢጤሥምኢ

በኢጤሥምኢ ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በየአስራ አምስት ቀኑ ዘወትር ማክሰኞ በኢንስቲትዩቱ ክንውኖች ላይ በማተኮር የሚታተም

ቅጽ 5 ቁጥር 5 ጥቅምት 30 ቀን 2006 ዓ.ም

## ሥነ ምግብ ከአየር መዛባትና ከሥርዓተ ጾታ ጋር ባለው ትስስርና ጉዳት ላይ ባለሙያዎች መከሩ

በኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት ሥነ ምግብና የአየር መዛባት ከሥርዓተ ጾታ ጋር ያለው ትስስርና የሚያስከትለው ጉዳት ላይ ያተኮረ የባለሙያዎች ውይይት ጥቅምት 20 ቀን 2006 ዓ.ም በድሪምላይነር ሆቴል አካሄደ፡፡



የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች በከፊል

የመድረኩ አዘጋጆች የሆኑት የዳይሬክቶሬቱ ባለሙያዎች እንደገለጹት ውይይቱ የተካሄደው ሥነ ምግብና የአየር መዛባት ከሥርዓተ ጾታ ጋር ያለውን ትስስር ለውይይቱ ተሳታፊዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥና እነርሱም ያላቸውን እውቀት ለሌሎች እንድያካፍሉ ለማድረግ ነው፡፡

በምግብና ሥነ ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት ተመራማሪ እና የውይይት መድረኩ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ማስረሻ ተሰማ እንደገለጹት በውይይት መደረኩ አራት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ተለይተው ነበር፡፡

እነዚህም በሥነ ምግብ፣ በአየር መዛባትና ሥርዓተ ጾታ ትስስር ላይ ግንዛቤ መፈጠር እና ይሄንኑም ተሳታፊዎቹ ከዕለት ተዕለት ሥራቸው ጋር

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## ሴቶች ህገ መንግስቱ ያጎናጸፋቸውን መብቶች መጠቀም እንዳለባቸው ተገለጸ

*በኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት የሥርዓተ ጾታና ሴቶችን የማብቃት ዳይሬክቶሬት በሥርዓተ ፆታ ጽንሰ ሃሳብ፣ የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ፣ በህገ መንግስቱ ለሴቶች የተሰጡ መብቶች እና ሲቪል ሰርቪሱ ያጎናጸፋቸው መብቶች ላይ ያተኮረ ሥልጠና ከኢንስቲትዩቱ ከተለያዩ ክፍሎች ለተወጣጡ ሠራተኞች ከጥቅምት 29-30 ቀን 2006 ዓ.ም በኢንስቲትዩቱ አዳራሽ ተሰጠ፡፡*

*በሥርዓተ ፆታና ሴቶችን የማብቃት ዳይሬክቶሬት የሥርዓተ ፆታ ኦፊሰር የሆኑት አቶ አለሽኝ ገዳሜ እንደገለጹት የሥልጠናው ዋና አላማ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ሥርዓተ ፆታን አስመልክቶ የነበረውን የተዛባ አመለካከት በማስወገድ*

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## በኢንስቲትዩቱ የሠራተኞች ክበብ ዓመታዊ በዓል ተከበረ

በየዓመቱ በኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ክበብ እና በኢንስቲትዩቱ ማኔጅመንት ቅንጅት የሚከበረው የሠራተኞች ክበብ ዓመታዊ በዓል ጥቅምት 23 ቀን 2006 ዓ.ም ተከበረ፡፡

የበዓሉ አዘጋጆች እንደገለጹት በዓሉ በየአመቱ መግቢያ ላይ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማካተት የሚከበር ሲሆን፣ ዝግጅቱም ሠራተኞችን እያዝናና ሥራቸውን በአዲስ መንፈስ እንዲጀምሩ ከማስቻሉም በላይ በሠራተኞች መካከል መልካም ቅርርቦሽ እና የሥራ መንፈስ እንዲኖር በማስቻል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

በውስጥ ገጾች፡ -

. ለግንዛቤዎ

# ሴቶች ህገ መንግስቱ ያጎናጸፋቸውን ...





የሥልጠናው ተሳታፊዎች በከፊል

የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ የልማት ጉዳይ ነው ብሎ የሚያስብ ዜጋን መፍጠር ሲሆን ሠራተኛው የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጅ አውቆና ተረድቶ የራሱንም ሥራ ቆርሶ ወስዶ የኢንስቲትዩቱን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት ዝግጁ ለማድረግ እንዲሁም ሁሉም በተሰማራበት የሥራ መስክ አንድ አይነት አመለካከትና የጋራ ራዕይ እንዲኖረው ለማድረግ ሲሆን በተለይም ሴቶች ይህንን አመች አደረጃጀት ተጠቅመው ለሥራቸው አመቺ የሥራ አካባቢ መፍጠር እንዲችሉ ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

አክለውም አቶ አለሽኝ ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 35 ለሴቶች ብቻ ያስቀመጣቸውን መብቶች ማወቅና መጠቀም እንዳለባቸው ጠቅሰው በተለይም ሴቶች በሥራቸው ላይ ጫና የሚፈጥሩ ነገሮችን በማስወገድ ለሥራቸው አመቺ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር ተደራጅተው መንቀሳቀስ እንዳለባቸውና እንዲህ አይነት አደረጃጀቶች መኖሩ ለሥራቸው የተሻለ ሁኔታ ይፈርጥላቸዋል ብለዋል፡፡

ሥልጠናው ህገ መንግስቱም ሆነ የሲቪል ሰርቪሱ መመሪያ ለሴቶች ከሰጣቸው መብቶች የአውንታዊ የድጋፍ እርምጃ፣ በወሊድ ጊዜ ሴቶች ከሙሉ ደሞዛቸው ጋር የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት፣ ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት እና ሌሎችንም መብቶቻቸውን ለራሳቸው ማወቅና መጠቀም እንዲሁም ሌሎች ሴቶችንም ለማሳወቅ እውቀቱ እንዲኖራቸው ለማድረግ የታሰበ ሥልጠና ነው፡፡

## ሥነ ምግብ ከአየር መዛባትና ከሥርዓተ ጾታ ጋር ባለው ትስስርና...

እንዲያያይዙት ማድረግ፣ ሥነ ምግብና የአየር መዛባት ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለውን ትስስር አሰመልክቶ እስካሁን ያለውን ግንዛቤ በተሻለ የግንዛቤ ደረጃ መለዋወጥ፣ ተሳታፊዎች ከውይይት መድረኩ የቀሰሙትን እውቀት ከየዕለት ተዕለት ሥራዎቻቸው ጋር እንዴት ማስተሳሰር እንደሚችሉ ዕቅድ ይዘው እንዲሄዱ ማድረግ እና ወደፊት ለሚሠሩ ሥራዎች የጋራ የትስስር መረብ መዘርጋት የሚሉ ናቸው ብለዋል፡፡

የውይይት መድረኩን በንግንግር የከፈቱት የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተወካይ ዶ/ር አዱኛ ወዬሳ እንደገለጹት ይህ አውደ ጥናት የተለያዩ ባለሙያዎችን ማለትም የሥነ ምግብ፣ የአየር ንብረት፣ የሥርዓተ ፆታ እና የግብርና ባለሙያዎችን አንድ ላይ የሚያገናኝና ሥነ ምግብ ከአየር መዛባትና ሥርዓተ ፆታ ጋር ያለውን ትስስርና የሚያስከትለው ጉዳት ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ መድረክ ነው፡፡

አክለውም ዶ/ር አዱኛ ይህ አይነት እውቀት ለመለዋወጥ የሚያስችል አውደ ጥናት መዘጋጀቱ የአገሪቱን ብሔራዊ የሥነ ምግብ ፕሮግራም በተቀናጀ መልኩ ለመተግበርና በተለያዩ ሙያ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሙያዎችን በምግብ ደህንነት፣ በሥነ ምግብ፣ በአየር ንብረት እና ሥርዓተ ፆታን ከመደገፍና ከመተግበር አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡

ውይይት መድረኩ የተለያዩ ባለሙያዎች ሥነ ምግብ ከአየር መዛባትና ከሥርዓተ ፆታ ጋር ያለውን ተያያዥነት እና የሚያስከትለው ጉዳት ላይ በተለያዩ አካባቢዎች የተካሄዱ የጥናት ውጤቶችን ያቀረቡ ሲሆን በእያንዳንዱ ገለጻ ላይም ውይይቶች ተካሂደዋል::

በውይይቱ ወቅት ጥናት ያቀረቡ ባለሙያዎች እንደገለጹት ሴቶች የአየር መዛባት በሚደርስበት ወቅት በሚከሰት የኑሮ ጫና ምክንያት የውሃ አቅርቦት እና የማገዶ እንጨት እጥረት ስለሚከሰት ለውሃ ፍለጋ እና እንጨት ለቀማ ራቅ ወዳሉ ቦታዎች ለመሄድ ስለሚገደዱ  ማህበረሰቡ ለሴቶች ከተወው ማህበራዊ የሥራ ጫና በተጨማሪ የየዕለት ኑሮዋቸው ላይም ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል፡፡

# በኢንስቲትዩቱ የሠራተኞች ክበብ...





ዶ/ር አመሃ ከበደ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር በዓሉን አስመልክቶ ንግግር ባደረጉበት ወቅት

በዓሉን በንግግር የከፈቱት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አመሃ ከበደ ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ግዜያት ለክበቡ ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸው ይህም ድጋፍ የክበቡ ዋና ዓላማ የሆነውን ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የምሳ አገልግሎት በማቅረብ ሠራተኞች ምሳ ፍለጋ የሚያጠፉትን ሰዓት በማስቀረት በሥራቸው ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል የሚለውን ለማሳካት ረድቷል ብለዋል፡፡

ዶ/ር አመሃ አክለውም ኢንስቲትዩቱ ካለፉት ጥቅት አመታት ጀምሮ ብዙ ኃላፊነቶችን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ካሉ በኋላ የአምስት ዓመቱን ስትራቴጅክ ዕቅድ በመንደፍ ትግበራውም ሦስት አመታትን አስቆጥሯል ብለዋል፡፡ የ2006 ዓ.ም





ሠራተኞቹ ግብዣ ላይ

አንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን በኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር አካላት ደረጃ ተገምግሞ አፈጻጸሙ 65 በመቶ እንደሆነ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በቀሪዎቹ የበጀት ዓመቱ ወራት የተሸለ ሥራ ተሰርቶ መልካም የሆነ ውጤት እንዲመዘገብ ሁሉም የኢንስቲትዩቱ ሠራተኛ በየሚገኝበት የሥራ እርከት ርብርብ እንዲያደርግ አሳስበዋል፡፡

ዶ/ር አመሃ አያይዘውም የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ለወደፊቱም አቅም በፈቀደ መጠን ክበቡን ለማጠናከር ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል፡፡

የ2006 ዓ.ም የሠራተኞች ክበብ ሊቀመንበር አቶ አንጀሎ አሻ በዚህ ዘንድሮ ለ39ኛ ጊዜ በሚከበረው በዓል ላይ ባሰሙት ንግግር የክበቡ ዋና ዓላማ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የምሳ አገልግሎትን ያለ ምንም ውጣ ውረድ በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ ነው ካሉ በኋላ ይህም ሠራተኞች በየጊዜው እያሻቀበ ያለውን የምግብ ዋጋ ንረት ተቋቋመው እንዲዘልቁ በመደጎም ላይ የተኮረ ነው ብለዋል፡፡



በጡረታ ለተገለሉ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ሥጦታ ስበረክትላቸው

አቶ አንጀሎ አክለውም የምግብ ማዘጋጃ ቦታው ኋላ ቀርና ለምግብ ዝግጅት አመቺ ባለመሆኑ ጥራት ወዳለው ዘመናዊ ማዕድ ቤት ደረጃ ለማሻገር ፕላኑ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መሐንዲስ መሰራት ስለነበረበት ወደዚያ የተላከ ቢሆንም ምላሽ ለማግኘት ረዥም ጊዜ በመወሰዱ በእቅዳችን መሰረት ማከናወን አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ የ2006 ዓ/ም ኮሚቴ የመጀመሪያ ሥራው እንደሚሆን ሁኔታዎች እንደሚያስገድዱ ገልጸው የክበቡ የበላይ ጠባቂዎችና ኃላፊዎችም በዚህ ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንዲያደርጉ በመላዉ የማህበራዊ ሻይ ቤት ተጠቃሚዎች ስም አደራ ብለዋል፡፡

በእለቱ የተለያዩ ዝግጅቶች የቀረቡ ሲሆን፤ በ2005 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱን በጡረታ ለተሰናበቱ ሠራተኞች እና ከኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች መካከል ተመርጠው በ2005 ዓ.ም ክበቡን ሲያገለግሉ ለቆዩ ሠራተኞችም በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አመሃ ከበደ አማካኝነት ስጦታ ተበርክቶላቸዋል፡፡

ለማህበራዊ ሻይ ቤት ሠራተኞችም ላደረጉት መልካም አገልግሎት በክበቡ የዓመቱ ሊቀመንበር በአቶ አንጀሎ አሻ አማካኝነት ሥጦታ ተበርክቶላቸዋል፡፡



# ለግንዛቤዎ

የኢትዮጵያ
የጤናና ሥነ ምግብ
ምርምር ኢንስቲትዩት

ዜና ኢጤሥምኢ

በኢትዮጵያ የጤናና ሥነምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በየአስራ አምስት ቀኑ ዘወትር ማክሰኞ የሚታተም

አዘጋጆች፡-
አቤል የሻነህ
ፍቃዱ በሻህ
ፀሐይነሽ ኤሊያስ

ፎቶግራፈር፡-
ሚሊዮን ከበደ

የኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
ሐረገወይን ይግዛው

+25112 751522
+25112 753470

+251 1 754744
+251 1 757722

1242/5654

ehnri@ethionet.et

## የጸረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ ስንል ምን ማለታችን ነው?

የጸረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ ማለት ከዚህ በፊት በበሽታ አምጪ ተህዋሲያን (ጀርሞች) አማካኝነት የሚመጡ በሽታዎችን ለማከም ወይም ለመከላከል ለህሙማን ሲሰጥ የነበረ አንድ ጸረ-ተህዋስ መድኃኒት፣ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ በነበረው መጠን ወይም ከዚያም በላይ የሰውነታችን ሴሎች ሊቋቋሙት በሚችሉት መጠን ሁሉ ለበሽተኛው ሲሰጥ ተህዋሲያኑ (ጀርሞቹ) የማይሞቱ ወይም መራባትን የማያቆሙ ከሆነ ተህዋሱ (ጀርሙ) ከመድኃኒት ጋር ተላምዷል ሲባል ሂደቱንም የጸረ-ተህዋሲን መድኃኒቶች መላመድ (Antimicrobial resistance) ይባላል።

የጸረ-ተህዋሲያን መድሃኒቶች በተላላፊ በሽታዎች አማካኝነት የሚከሰት ህመምና ሞትን በመቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ለወባ፣ ቲቢ፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ለሚተላለፉ በሽታዎች፣ ለታይፎይድ፣ እና ሌሎች በሽታዎች የሚውሉት መድሀኒቶች ተህዋሲያኑን የመግደል ተግባራቸውን እያቆሙ እና መድሃኒቱንም እየተለማመዱ መምጣታቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚሁ ዓይነት መድሀኒቱን መላመድ ማለት የተህዋሲያኑ በሽታውን ለማከም ከሚውሉት መድሀኒቶች ውስጥ ከተወሰኑት ጋር መላመድ እና አለመጥፋት ማለት ነው። ባክቴሪያው እነዚህን መድሀኒቶች ተለማምዶ አልሞት ሲል መድሀኒቱን የተለማመደ ይባላል። ይህም በአብዛኛው የሚከሰተው አንድ ታካሚ በምርመራ በሽታው እንዳለበት ታውቆ የታዘዘለትን መድሀኒቶች በአግባቡ ሳይወስድ ሲቀር ነው።

በአግባቡ ህክምናን ካለማድረግና መድሃኒቶችን ከማቋረጥ የሚከሰቱ በሽታዎች ለህክምና አሰጣጥ አስቸጋሪ ናቸው። የቲቢን በሽታ ስንመለከት በአሁኑ ሰዓት ቲቢን ለማከም ሪፋምቢሲንና ሀይዞኒአይዚድ የተባሉ መድኃኒቶችን የሚንጠቀም ሲሆን ባክቴሪያው እነዚህን መድሀኒቶች ተለማምዶ አልሞት ሲል ኤም ዲ አር ቲቢ ወይም መድሃኒቱን የተላመደ የቲቢ በሽታ ይፈጠራል። ኤም ዲ አር ቲቢ ወይንም መድሀኒቱን የተለማመደ ቲቢ ስንል በሽታው ቲቢን ለማከም ከሚውሉት ከተወሰኑት መድሀኒቶች ጋር የተለማመደ ወይንም የቲቢ ባክቴሪያው እነዚህን መድሀኒቶች ተለማምዶ አልሞት ሲል ማለት ነው።

በአለም ላይ በአመት 440 ሺ አዳዲስ መድኃኒቱን በተለማመደ የቲቢ በሽታ የተያዙ በሽተኞች እንደሚኖሩና ከእነዚህም መካከል 150 ሺ የሚደርሱት ለሞት እንደሚዳረጉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

መድኃኒቶች በባለሙያ በታዘዘው መጠንና ሰዓት ከተወሰዱ ፈውስ እንደሚሆኑ ሁሉ ይህ ካልተጠበቀ ደግሞ ለበለጠ በሽታ ያጋልጡናል። ብዙን ጊዜ ከመድኃኒት አወሳሰድ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ስህተቶች ኅብረተሰቡን ለበለጠ ጉዳት ሲያጋልጠው እየታየ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል ጊዜ ያለፈባቸውን መድኃኒቶች መጠቀም፣ ለአንድ ሰው የታዘዘውን መድኃኒት ለሌላ ሰው ማካፈል፣ ተመሳሳይ የበሽታ ምልክት ነው በማለት አንዱ የሌላውን ህሙማን መድኃኒት መጠቀም፣ ቶሎ ለመዳን በማሰብ ከታዘዘው መጠን በላይ መውሰድ፣ መድኃኒትን ጀምሮ ማቋረጥ፣ በታዘዘው ጊዜና ሰዓት አለመውሰድ እና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ትክክለኛ የመድኃኒት አጠቃቀም ስንልም ትክክለኛ መድኃኒት በትክክለኛው ሰዓት መጠቀም፣ በትክክለኛ ዋጋ መግዛትና በትክክለኛ መጠን መውሰድን ሊያካትት እንደሚገባ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።